ከጥቁር መልበሱስ በኋላ?

ከሁለትና ሶስት ቀን ጥቁር መልበስ በኋላ business as usual ብሎ ሁሉም ወደየጎሬው መግባት ነው? ወይስ መሬት የያዘ ተከታታይ ህዝባዊ ትግልና ተቃውሞ ነው የሚደረገው?

ከልና ማቅ ለሁለት ቀን ለብሶ ለመበተንማ፥ ጠላት ብአዴን ከአመት አመት እያስጠቃን ባንፈልግም ጥቁር እያስለበሰን እኮ ነው!!!

የአማራን ህዝብ ጥቁር አስለብሶና ህዝብን አነሳስቶ ሲያበቁ፥ ከሁለት ቀን በኋላ ማፈግፈግ ፥ መቼም ይቅር የማንለው ባንዳነት ነው።

ሁለት ቀን ከልና ማቅ አስለብሶ፥ በሳልስቱ business as usual አይነት አካሄድ፥ የታፈነ የህዝብ ስሜትን ለማስተንፈስ እንደ relief valve የመጠቀም ፖለቲካዊ ሸፍጥ ነው። ይህ ማለት አማራን predictable ህዝብና ልክ እንደ ጥቁር አሜሪካዊያን ትግል ከቁራዊ ጩኸት ያልዘለለና መቼም ውጤት የማያመጣ ያደርገዋል።

ልብ ሰባሪው ሀዘናችንን በጊዜ ቋጭተን ወደ ትግል አብዮት ማማ መሄድ እንጂ ማፈግፈግ የለም!!!

- በሁለት ሀሳብ የሚያነክስ ወደኋላ ይመለስ!!!

- አፉ ከእኛ፥ ልቡ ከእነኛ ጋር የሆነ የጠላት ብአዴን ተላላኪ ወደኋላ ይመለስ!!!

- የሻማ ማብራት፣ ጥቁር መልበስ፣ ወዘተ በራሳቸው የቆሙ የትግል አይነት አይደሉም። እንዲያውም ceremonial ናቸው። ጥቁር በመልበስ ህብረታችንን እናሳይ፣ መጠቃታችን አሰባስቦናል ለማለት ይረዳል። ጥቁር መልበሳችንና መሰባሰባችን ትርጉም የሚኖረው ግን፥ ይህ የተሰባሰብንበትን መንፈስና Cause ከፍ ወዳለ የፖለቲካ ትግል ስናሳድገው ብቻና ብቻ ነው!!! ከዚያ ውጪ የአማራን መከራ ማራዘምና ለጠላትም "ተንጫጭተው ዝም ይላሉ" የሚል አደገኛ መልዕክት የሚያስተላልፍ ነው።

ወገብን ጠበቅ አድርገን ወይ አማራን የምትሸከም ሀገርና መንግስት እንዲፈጠር፥ አይ አማራን መሸከም አልችልም የምትል ከሆነ ደግሞ አፈራርሰናት እኛን የሚመስል የራሳችንን አባት ሀገር እንመሰርታለን!!!

"ይሆናል ብለን ወፍ አጠመድን፣
ሳይሆን ሲቀር ግን ፈትተን ለቀቅን።" እንደሚባለው ነው። የአብይ አህመድ መንግሥት ኢትዮጵያ ከወያኔዋ ኢትዮጵያ የቀጠለች፣ በአማራ ደም መስከሯም እየከፋ ነው የመጣው።

የሁለቱም ዘመን ተላላኪና አስጠቂያችንም በጉያችን ያለው ብአዴን ነው። በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ብአዴን፣ የፖለቲካና የኢኮኖሚ መዋቅሩ መመታት አለበት። ሞታችን እንኳን የሮናልዶን ወለምታ ያህል በዚያች ሀገር ውስጥ ሰውን የሚያስደነግጥ እንዳሆን ያደረገው ብአዴን ነው!!! አንዴ አይደለም ሺህ ጊዜ ከላይ እስከታች መጠረግ አለባቸው!!!

አብይ አህመድና እሱ የሚመራው መንግሥት በአማራ ደም ዋነኛ ተጠያቂ ነው። ሀገረ መንግስቱን ሲረከብ፥ ፓርክ ለመስራትና ችግኝ ለመትከል ሳይሆን በቀዳሚነት የዜጎችን ደህንነት ለማስጠበቅ ነው። "ለውጡን የማይፈልጉ ሀይሎች" የሚላቸው ሰበብ እንጂ ዋነኛ ፈፃሚው ራሱ አብይ አህመድ ነው። የመንግስትን መዋቅር ተቆጣጥረህ ስታበቃ፥ መንግስታዊ መዋቅር ቢያንስ በሀገር አቀፍ ደረጃ የሌለው ቡድን ፥ ሶስት አመት ሙሉ ጥቃት ፈፀመ ስትል፥ ድንቁርናህን ለማስመስከር ካልሆነ በቀር አንተ ከበሻሻ መጥተህ ማንንም ልታታልል አትችልም።

ለሶስት አመት ሙሉም በዚህ ረገድ፥ እንደሚባለው ወያኔ ስፖንሰር የሚያደርገው ቡድን ጥቃት እየፈፀመና ሀገረ መንግስቱን የተቆጣጠረው ሀይል ደግሞ ማስቆም ካልቻለ፥ ሀገር መምራት ሳይሆን አትክልተኛነቱን አጥብቆ ቢይዝ ለሁሉም መልካም ነው።

እውነታው ግን ይህ አይደለም!!! የእስከዛሬው የአማራ ጥቃት በከፍተኛ ጥንቃቄና ዕቅድ አብይ አህመድ በበላይነት እየመራ የሚያስፈፅመው፥ አማራን የማፅዳትና፥ አማራን በማያቋርጥ ቀውስ በመማገድ ዕረፍት እየነሱ የማዳከም፥ ጎን ለጎንም ወይ ኦሮሞነት የገነነባት ኢትዮጵያን አልያም ነፃዋን "ኦሮሚያ" የተሰኘችን ሀገር የማዋለድ ፕሮግራም ነው።

ለዚህ ደግሞ ብአዴን አማራን በማስመታት ተባባሪ ሆኖ ይገኛል።

አሁን ከሞላ ጎደል ሁሉም ነገር ግልጽ ነው። አማራ መንግስት አልባ ህዝብ ነው፤ በዚህም ሳይወሰን ከመቼውም ጊዜ በከፋ ሁኔታ እየታረደ ይገኛል። ይህ መቆም የሚችለው በተሰነዘረብን ጥቃትና በገጠመን ፈተና ልክ መሬት የያዘ የማያቋርጥ ትግል ስናደርግ ብቻ እንጂ በሁለትና ሶስት ቀን ዘመቻ ነገሮች ወደነበሩበት እንዲመለሱ በማድረግ አይደለም!!!

የገጠመን የተፈጥሮ አደጋ አይደለም፥ ሁለት ቀን ጥቁር ልብስ ለብሰን፥ ከዚያም ወደየጉዳያችን የምንበታተነው!!!

በሁለት ሀሳብ የሚያነክስ ፥ ወደኋላ ይመለስ!!!

ዴቭ ዳዊት።